DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS




www.dcps.dc.gov


ጥያቄዎች አሉዎት? በቀጣዩ አድራሻ ያግኙን
(202) 719-6613 ወይም ofpe.info@dc.gov.

1200 First Street, NE, Washington, DC 20002

/dcpublicschools @dcpublicschools @dcpublicschools

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ



# የክፍል ደረጃ K



# የወላጅ ስርዓተ ትምህርት መምሪያ የአጠቃቀም መንገድ፣

ይህ መምሪያ ልጅዎን በቤት ውስጥ ለማገዝ የሚያስፈልጉዎትን መሳሪያዎች ይሰጥዎታል። በዚህ የመረጃ ጥራዝ ውስጥ፣ ልጅዎ የትምህርት ግቦቹን እንዲያሳካ ለማገዝ እንዲችሉ በ DCPS ስርዓተ ትምህርት ላይ የተመሰረቱ ስትራቴጂዎችን ያገኛሉ። ልጅዎ በት/ቤት ውስጥ የሚማረውን ትምህርት እና በተጨማሪም በቤት ውስጥ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ጥሩ ግንዛቤ ይጨብጣሉ/ያገኛሉ፡፡

## እርስዎ ማድረግ የሚችሉት፣

በልጅዎ አካዳሚክ ብቃት ላይ እርስዎ ወሳኝ ሚና ይጫዎታሉ። በቤት ውስጥ ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ እነዚህ የተወሰኑ አስፈላጊ ነጥቦች ናቸው፡

- ትምህርት የስኬት መሰረት መሆኑን ልጅዎ እንዲያውቅ ያድርጉ።
- ልጅዎ መዋእለ ህጻናት ውስጥ ምን ይማራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ይወቁ።
- ልጅዎ ከፍተኛ የሆኑ የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ አካዳሚያዊ ግቦችን እንዲያሰቀምጭ ያግዙት።
- የቤት ስራ በተገቢው ሰአት እና በአግባቡ እንዲያጠናቅቅ በቂ ጊዜ ይስጡ፡፡
- በት/ቤት ውስጥ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ከልጅዎ ጋር በመነጋገር ሒደታዊ ለውጦችን ያለማቋረጥ ይከታተሉ።
- ለልጅዎ ይሟገቱ።
- የልጅዎን ጥንካሬ ከመምህሩ ጋር ይጋሩ፡፡

## የልጅዎን መምህር መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፣

ከልጅዎ መምህር ጋር በሚወያዩበት ጊዜ ስለ ልጅዎ የትምህርት አቀባል እና ሁኔታ ላይ ትኩረት እያደረጉ ቀጥሎ የተመለከቱትን ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡

- የመማር ግቦች ምንድን ናቸው? የመማር ግብ አስመልክቶ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች እንደ ምሳሌ ሊነግሩኝ ይችላሉ?
- የልጄን ስራ እንደ ምሳሌ ማየት እችላለሁ? እነዚህን የመማር ግቦች የሚያሳካው ወይም የማያሳካው እንዴት ነው?
- ልጄ በትምህርቱ እያለ/ ከሆነ ደረጃ በላይ ሲዘልቅ ሌላ ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ የሚገባኝ ምንድናቸው? ቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላሁ?
- ቤት ውስጥም መተግበር ያለባቸው የመማሪያ ክፍል ውስጥ መደበኛ ተግባራት ምንድን ናቸው?
- የእርስዎን ክፍለ ጊዜ በተመለከተ ለልጄ በየቀኑ ማቅረብ ያለብኝ ጥያቄዎች ምን ዓይነት ናቸው?

## ከልጅዎ ጋር መነጋገር፣

ጥሩ ጭውውቶች ልጆቻችን በሕይወታቸው ውስጥ እኛ እንደሚያገባን እንዲያዩ ያግዛሉ። እነዚህ ከልጆችዎ ጋር መልካም ውይይት በሚያደርጉበት ጊዜ በቅድሚያ መጠየቅ የሚያስፈልጉ ጥያቄዎች፡

- እስኪ በቀንህ ውስጥ ምርጥ ስለምትለው ጊዜ አውራኝ።
- በውሎህ ውስጥ ያጋጠመህ እጅግ በጣም ፈታኝ ነገር ምንድነው?
- ዛሬ ከተማራችሁት ውስጥ አንድ ነገር ልታሳየኝ ትችላለህ?
- ት/ቤት ውስጥ የምታነቡት መፅሐፍ ምንድን ነው? የምትወደውን መገለጫ ባህርይ ብትነግረኝ? ይህን መገለጫ ባህርይ የምትወደው ለምንድን ነው?
- በት/ቤት ውስጥ ከዚህ በላይ መስራት አለብኝ የምትላቸው ነገሮች ምንድናቸው? በአነስተኛ መጠን ማድረግ አለብኝ ብለህ የምታስበውስ ምንድን ነው? ለምን?

# የአፀደ ሕጻናት ተማሪዬ እየተማረ ያለው ነገር

| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ |
|---|---|---|---|---|
| የበልግ ወቅት | ተማሪዎች ጥሩ ጓደኛ ስለመሆን፣ ልዩነቶችና ተግዳሮቶችን ስለማሸነፍ፣ ሌሎች ሰዎችን ራስህ ለመታየት በምትፈልገው መንገድ ማየትና ነባር ባሕሎችን ከአዳዲስ ጓደኞች ጋር ማቆየትን በተመለከተ ይማራሉ።<br>• • •<br>ተማሪዎች የኮሙኒቲ ሰራተኞችና የቡድን ስራ የማንኛውም ማህበረሰብ ወሳኝ ክፍሎች መሆናቸውን ይማራሉ። ሰዎች የሚኖሩበት መንገድና ቦታ እነርሱ በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ የሚሰሩበትን፣ የሚጫወቱበትንና የሚኖሩበትን መንገድ እንዴት እንደሚመለከት ይዳስሳሉ።<br>• • •<br>ተማሪዎች የተለያዩ ዓይነት የአየር ሁኔታዎች እንዳሉ ይማራሉ፤ የአየር ሁኔታ በሰዎችና በአካባቢ ላይ ስላለው ተጽእኖ እና የአየር ሁኔታን ስለመመዝገብና ስለመከታተል ይማራሉ። | ተማሪዎእ እስከ አስር ድረስ መቁጠር፣ እስከ አስር ያሉ ቁጥሮችን ከተዛማጅ የዕቃዎች ብዛት ጋር ማዛመድና ቁጥሮችን በ10 ውስጥ ወደ ቁጥር መከፋፈልን ይማራሉ።<br>• • •<br>ተማሪዎች 2D እና 3D ቅርጾችን ይዳስሳሉ። ቅርጾችን በመለየትና በመግለጽ በቅርጾች መካከል ያሉ ተመሳሳይነቶችና ልዩነቶችን ለመግለጽም ኢ-መደበኛ ቋንቋ ይጠቀማሉ። | ተማሪዎች ሃይልን መጠቀም የአንድን ነገር እንቅስቃሴ እንዴት ሊቀይር እንደሚችል ይማራሉ።<br>• • •<br>ተማሪዎች የአየር ሁኔታዎች፣ የአየር ሁኔታ ፓተርኖችና የፀሐይን ተጽእኖ ይማራሉ። | ማንም ሰው ጀግና መሆን ይችላል? ተማሪዎች ተጨባጭና ልቦለዳዊ የሆኑ ጥሩ መሪዎችና ዜጎች መኖራቸውንና እንዲህ ለማለት የተቻለውም ባላቸው የተወሰኑ ብቃቶች ምክንያት መሆኑን ይማራሉ።<br>• • •<br>ስራዎች ያስፈልጉናል? ተማሪዎች ሰዎች በተለያዩ አውዶች ውስጥ የሚሰሯቸው የተለያዩ ዓይነት ስራዎች መኖራቸውን በመማር ሰዎች በጀት የሚያደርጉባቸውን መንገዶች ይተነትናሉ። |
| የክረምት ወቅት | ተማሪዎች ታሪኮች የሚጻፉት በገጸ ባህርያት፣ ማዕቀፍና ችግርና መፍትሔ ባላቸው ዋና ዋና ክስተቶች እንደሆነና ደራሲያንም ገጸ ባህርያትን የሚመለከቱ መረጃዎችን እንደሚያስተላልፉ ይማራሉ። የሕይወት ተሞክሮዎቻችን ለማጋራት ወደምንፈልጋቸው ታሪኮች ይመሩናል።<br>• • •<br>ተማሪዎች የሰው ልጅ ምድር ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ተዕእኖዎችን እንደሚያሳድርና ምድርን የመጠበቅ ሃላፊነቱ የእኛ መሆኑን ይማራሉ። የጥበቃ መንግዶችንም ያጠናሉ - መቀነስ፣ ዳግም መጠቀም፣ ሪሳይክል - እና ምድርን ለመጠበቅ የሚያስሉ መንገዶችን መተግበር፣ ለምሳሌ ምርቶችን ሪሳይክል በማድረግና ዳግም በመጠቀም። | ተማሪዎች እስከ 10 ያለ ቁመት፣ ክብደት፣ ችሎታና ቁጥሮችን ያወዳድራሉ።<br>• • •<br>ተማሪዎች እስከ 10 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን ይደምራሉ፣ ይቀንሳሉ። | ተማሪዎች ተክሎች እና እንስሳት በዙሪያቸው ካለ አካባቢ እንዴት ፍላጎታቸውን እንደሚያሟሉና የሰው ልጅ በአካባቢ ላይ ስለሚያሳድረው ተጽእኖ ይማራሉ።<br>• • •<br>ተማሪዎች ሕይወት ያላቸው ነገሮች ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዴት ከአካባቢያቸው ጋር እንደሚገናኙ ይማራሉ። | አሜሪካን ልዩ የሚያደርጋት ምንድን ነው? ተማሪዎች የቀን መቁጠሪያን በማጥናትና በተለያዩ ጽሑፎች ውስጥ በመሳተፍ ከዩናትድ ስቴትስ ጋር ብቻ የተያያዙ የበዓል ቀናትና ምልክቶችን ያጠናሉ። |
| የፀደይ ወቅት | ተማሪዎች ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የመጡ ሁለት ሰዎች የተለያዩ ተሞክሮዎችን እንደሚጋሩና እርስ በርስ ለመገናኘት እንደሚችሉ ይማራሉ። በዓለም ዙሪያና በተመሳሳይ ማህበረሰብ ውስጥም የተለያዩ ባህሎች አሉ።<br>• • •<br>ተማሪዎች የተክሎችን፣ የቢራቢሮዎችና በውሃና በምድር ላይ የሚኖሩ እንስሳትን የሕይወት ኡደት ይገነዘባሉ፤ ተክሎችና እንስሳት ወቅት ተኮር ለሆኑ ለውጦች እንዴት እንደሚዘጋጁም ይማራሉ። | ተማሪዎች ቁጥሮችን በአስርና ከዚያ በላይ በመፍታት የቦታ ዋጋን ይማራሉ። በአንድ እና አስር ቤት እስከ 100 ድረስ በመቁጠር ቅርጾችን ማዘጋጀትና መስራት ይችላሉ። | የት ነው ያለሁት? ተማሪዎች ካርታዎችና ሉሎችን በመጠቀም ስለ አድራሻ እና አቅጣጫ ግንዛቤያቸውን ያሳያሉ። | |

# ከአፀደ ሕጻናት ተማሪዬ ጋር የማከናውናቸው ተግባራት

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

**በየቀኑ ለ20 ደቂቃ ያህል አብራችሁ አንብቡ።**

## የበልግ ወቅት

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት**

ከአዳዲስ ጓደኞች ጋር ማድረግ የሚችሏቸውን አዝናኝ ተግባራት ዝርዝር በማውጣት ስዕል ይሳሉ። ዝርዝሩን ቤትዎ ውስጥ በመለጠፍ ተግባራቱ ሲከናወኑ ዙሪያቸውን ያክብቡ።

•••

በማህበረሰብዎ ውስጥ ያሉ ትጉህ ሰራተኞችን ይመልከቱ! ምን ዓይነት ስራ ነው እየሰሩ ያሉት? የታዘቧቸውን የተለያዩ ስራዎች በተመለከተ አዝናኝ ወይም አሰቸጋሪ ሊሆኑ በሚችሉት ነገሮች ላይ ተወያዩ።

•••

ዜና ላይ የአየር ሁኔታ ዘገባን ይከታተሉና አካባቢዎ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት የሚኖረውን የአየር ሁኔታ ይከታተሉ። በመጨረሻም፣ የራስዎን የአየር ሁኔታ ዘገባ አዘጋጅተው ለጓደኞችና ቤተሰቦች ማጋራት ይችላሉ! በእነዚያ ቀናት የነበረውን የአየር ሁኔታ የሚያሳዩ አንዳንድ ምስሎች ማካተትዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

**ሒሳብ**

ልጅዎ 4 ካልሲዎች ወይም 7 ቁልፎች እንዲያመጣልዎ በመጠየቅ የብዛት መጠኖችን እንዲለይ ያግዙት።

•••

የተለያዩ ቅርጾችን የሚመስሉ የተጨባጩ ዓለም ዕቃዎችን ይፈልጉ። ልጅዎ በክፍሉ ውስጥ ያለ ክብ ወይም አራት ማዕዘን ነገር የሚመስል ዕቃ መፈለግ እንደሚችል ይጠይቁት።

**ሳይንስ**

ከልጅዎ ጋር ከቤት ወጥተው የእግር ኳስ በእግርዎ ይምቱ። የበለጠ ወይም ያነሰ ጉልበት መጠቀም (ለምሳሌ፡ ኳሱን በደንብ ወይም ቀለል አድርጎ መምታት) ኳሱ በሚጓዝበት ሁኔታ ላይ ሊገመት የሚችል ውጤት ያለው መሆኑን ያሳዩት።

•••

ከቤት ውጭ የእግር ጉዞ በማድረግ ስለ ዕለቱ የአየር ሁኔታ ተወያዩ። ሕንጻዎቻ ከተለያዩ የአየር ሁኔታዎች እንዲጠብቁን ተደርገው ስለተገነቡባቸው መንገዶች ልጅዎ እንዲያስብ ያበረታቱት።

**የማበልጸጊያ ተግባር**

በየቀኑ በማንበብ ስንት ሰዓት እንዳነበብክ የማንበቢያ መመዝገቢያ ዲያሪ ይጠቀሙ:: በመጠኑ በመዘርዘር የምትወዳቸውን ባህሪያት ከእያንዳንዱ ታሪክ መውሰድ:: የሚያደንቁትን የገጸ ባህርይ ልዩ ጠባዮች ያካትቱ።

•••

ሶስት አዳዲስ መጻሕፍትን ለማየት በአቅራቢያዎ ያለውን ቤተ መጻሕፍት ይጎብኙ! በአካባቢ የሚገኘውን መጽሀፍት ቤት ቅርንጫፍ ለማግኘት bit.ly/findmylibrary የመረጃ መረባችንን ይጎብኙ::

## የክረምት ወቅት

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት**

ወደ ፓርክ ስለሚደረግ ጉዞ አዝናኝ ታሪክ ጽፈው በማሳየት ቤተሰብዎን በዋና ገጸ ባህሪነት ያስቀምጡ! በፓርኩ ውስጥ የነበረዎትን አዝናኝ ጊዜ አስመልክቶ አስገራሚ ምስሎችን መሳልዎትን እርግጠኛ ይሁኑ።

•••

ቤተሰብዎ ሪሳይክል ያደርጋል? አዎ ካሉ፣ የተወሰኑ ነገሮችን እንዴት በድጋሚ መጠቀም እንደሚችሉ ያስቡ። ለምሳሌ፣ የወረቀት ጀርባ ማቅለሚያ ወረቀት ሊሆን ይችላል ወይም በሶፍት ወረቀት ጥቅል ሮኬት መስራት ይችላሉ። ካልሆነ፣ ጣሳ፣ የብርጭቆ ጠርሙስ እና ወረቀት የሚሰበስቡበት ሪሳይክል ማድረጊያ ክፍል ያዘጋጁ።

**ሒሳብ**

ልጅዎን ከባድ ወይም ቀላል የትኛው እንደሆነ በመጠየቅ ወይም የትኛው ዕቃ ረዥም እንደሆነ በመጠየቅ ስለ ንጽጽር ከልጅዎ ጋር ይወያዩ።

**ሳይንስ**

ልጅዎ በመኖሪያ አካባቢያችሁ (እና በዚያ በሚኖሩ ተክሎችና እንስሳት ላይ)ላይ የሚያደርሱትን አሉታዊ ተጽእኖ ለመቀነስ ስለሚያስችሉ መንገዶች እንዲያስብ ይጠይቁት።

•••

አንድ እንስሳ በመካነ እንስሳት ውስጥ ወደ አዲስ ማሳያ ከመሄዱ አንጻር የመኘታ ሰዓት ተረት ያዘጋጁ።

**ማህበራዊ ሳይንስ**

ቤት ውስጥ በጋራ ቦታ ላይ ካሌንደር ያስቀምጡና ካሌንደሩን በማንበብ ለቤተሰብዎና ለማህበረሰቡ ወሳኝ የሆኑ ቀናት ላይ ምልክት ያድርጉ። ልጅዎ በክፍል ውስጥ የተማረውን ምልክቶች በበዓላት ቀናት ላይ እንዲያደርግ ይጠይቁ፤ ለምሳሌ Martin Luther King, Jr. Day በጃንዋሪ፣ President's Day በፌብሩዋሪ እና Emancipation Day በኤፕሪል

**የማበልጸጊያ ተግባር**

እንደ የልደት ቀን፣ የበዓል ቀናት የመሳሰሉ ልዩ ቀናትና ሌሎች ወሳኝ ቀናትን ዝርዝር ይያዙ። ከዚያም ከልጅዎ ጋር ሆነው በካሌንደር ቅደም ተከተል ያስቀምጡ።

•••

ዘወትር ማክሰኞ Smithsonian Museum of Natural History's Butterfly Pavilion በነጻ መጎብኘት ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ www.mnh.si.edu ይጎብኙ።

## የፀደይ ወቅት

**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት**

በሌላው የዓለም ክፍል ስለሚኖር ቤተሰብ አጭር ታሪክ ጽፈው ያሳዩ። ምን እንደሚበሉ፣ የት እንደሚኖሩና የት ት/ቤት እንደሚማሩ እና/ወይም ምን ዓይነት አልባሳት እንደሚለብሱ ዝርዝር መረጃ ያካትቱ።

•••

ቢራቢሮዎች አስደናቂ ናቸው! በጠርዙ አካባቢ የቢራ ቢሮን የተለያዩ ደረጃዎች ክብ ስዕል በመሳል ያሳዩ። ከዚያም በመጽሔት ወይም ኦንላይነ ላይ የቢራ ቢሮ ምስሎችን ፈልገው በፈጠራ ስራዎችዎ ውስጥ ያስገቡ!

**ሒሳብ**

በ10 ውስጥ የቁጥር ጥምሮችን መፈለግን ይለማመዱ። ልጅዎ 10 ቁጥርን ለማምጣት 4 ቁጥር ከማን ጋር እንደሚጣመር ይጠይቁ። ወይም 10 ቁጥርን ለማምጣት 7 ቁጥር ከማን ጋር እንደሚጣመር ይጠይቁ።

•••

ከልጅዎ ጋር በአስር እና በአንድ ቤት እስከ 100 ድረስ መቁጠርን ይለማመዱ። ቅርጽ ያላቸውን ነገሮች ለመፍጠር ስእሎችን ይሳሉ። ለምሳሌ፣ ሶስት ማዕዘን ጣሪያ እና ካሬ ቅርጽ ያለው መሰረት ላይ ያረፈ ቤት ይሳሉና ስለተፈጠረው አዲስ ቅርጽ ተነጋገሩ።

**ማህበራዊ ሳይንስ**

በጂፒኤስ ወይም በሜትሮ ላይ የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የአውቶብስ ምልክቶች፣ ወይም የሜትሮ ምልክቶች ወይም ካርታዎችን መመልከትዎን ይለማመዱ። ወዴት መሄድ እንዳለብን እንዴት እንደሚነግሩን ተወያዩ። ግራ፣ ቀኝ፣ ቅርብ፣ ሩቅ እና ለምሳሌ የከተማ የማዕዘን መለኪያ የመሳሉ ካርዲናል አቅጣጫዎችን ለማመልከት መግለጫዎችን ይጠቀሙ።

**የማበልጸጊያ ተግባር**

National Cherry Blossom Festival bit.ly/DCPSCherry ይጎብኙ።

•••

Kenilworth Park and Aquatic Gardens' Water Lily and Lotus festival ይጎብኙ። በኩሬ ወይም በተጠራቀመ ውሃ ውስጥ እንቁራሪቶችን ከፈለጉ በየሳምንቱ መጨረሻ ከ10 ኤ.ኤም ጀምሮ Visit bit.ly/DCPSKen ለተጨማሪ መረጃ ይጎብኙ::

•••

የበጋ ወቅት ዕቅዶችዎ ምን ምን ናቸው? በበጋው ወቅት መማራሁን ለመቀጠል በጋራ ልትሰሯቸው የምትችሉ አምስት ተግባራት ላይ ጥልቅ የሃሳብ ልውውጥ አድርጉ።

---

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት | ሒሳብ | ሳይንስ | ማህበራዊ ሳይንስ | የማበልጸጊያ ተግባር